# ያለፈው ወደፊት

አብርሃም በየነ

የሰማይ ላይ ህንጻ ስንቱን የማረከ

ዝናው ባጭር ጊዜ ሺህ ያንበረከከ

ገንብተን ነበረ ፍጹም ሰማይ ጠቀስ

ሰማየ-ሰማያት በስጋና በነብስ፤

ግን የመሃንዲሶች እሳቤ ሲፋለስ

እያነጹ አፍራሾች ሲንዱ ሲንዱ

ለመሆን አበቁት ከፈረሱት አንዱ።

ለሰማዕታቱ- TOWER in THE SKY

* *

ይምስለናል እንጂ ዘመን ሁሉም ህልፊት

ከኋላ የተውነው ሁነትና ድርጊት

ተመልሶ መጭ ነው ያለፈው ወደፊት፤

ትናንት ቢመስለንም በሽኝት ተጉዟል

ግን መልሶ መጭ ነው የነገን ቁልፍ ይዟል።

* *

ግፍ እያስቆጠረ ለዘሩ እያደላ

ቆይቶ የዕጁን ሲይገኝ የኋላ የኋላ

ሌላ ቀን መጥቶ ለከፋው ሲከፋ

እፈራለታለሁ ስሜን እንዳይጠፋ።

* *

እነህ ባለቀኖች ከታሪክ ቢማሩ

ፍቅር ኢያዘምሩም ጥላቻ እየዘሩ።

*                *

ቢጠሩት ላይሰማ በተነስ ቋንቋኛ

አንዱን ጆሮ ለብሶ ባንደኛው የተኛ

እንዲህን አገሬን በርዶታል ከፉኛ?

ሰኔ 2005